በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.219132

ጥቅምት 29/2015 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ዓለሙ ኤጀርሳ

ተጠሪዎች፡
1. አቶ ኤጀርሳ ገረሙ
2. አቶ ወርቁ አበበ
3. አቶ ኪሱ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን አመልካች ተጠሪዎችን ጨምሮ በአምስት ሰዎች ላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ፍሬ ሀሳብ ከወላጅ አባታቸው በውርስ የተላለፈላቸውን ቦታ እና አዋሳኛቸው በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከቱትን የእርሻ መሬት፣ የባህርዛፍ ተክል መሬት፣ የግጦች መሬት እና መኖሪያ ቤት የነበረበትን ይዞታ ተከሳሾቹ ምንም መብት ሳይኖራቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከ2006 ዓ.ም ጅምሮ 3 ሄክታር የሚሆን የባህርዛፍ መሬት እና 1 ሄክታር የሚሆን የግጦሽ መሬት፤ 2ኛ ተጠሪ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ 1 ሄክታር የሚሆን የእርሻ መሬት፤ 3ኛ ተጠሪ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ 1 ሄክታር የሚሆን የባህርዛፍ መሬት፤ እንዲሁም በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ያልተጠሩት 4ኛ እና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

4ኛ ተከሳሾች የአውራሻቸው የመኖሪያ ቤት የነበረበትን 1000 ካሬ ሜትር ይዞታ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገድደው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ሁሉም ተከሳሾች ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና አማራጭ የሥረ ነገር ክርክር አቅርበው መቃወሚያው ታልፏል፡፡ በአመራጭ የስረ ነገር ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን ይዞታዎች አመልካች በጠቀሱት ሁኔታ የያዙት ሳይሆን እያንዳንዳቸው በ1982/1983 አግባብ ካለው የመንግስት አካል በምሪት አግኝተው ግብር ሲገብሩበት ቆይተው በ1996 ዓ.ም ደግሞ በስማቸው ተመዝግቦላቸው ይዘው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ “ልንለቅ አይገባም” በማለት ተከራክረዋል፡፡ 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የነበሩት ደግሞ ክስ የቀረበበትን ይዞታ 4ኛ ተከሳሽ ቀደም ብለው በ2003 ዓ.ም ከሌላ ሰው ላይ ገዝተው ለ5ኛ ተከሳሽ በሽያጭ አስተላልፈው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የያዙት እንጂ በህግ ወጥ መንገድ ያልያዙት መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ሞግተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የሰው ምስክር ሰምቷል፡፡ በተጨማሪም ክስ የቀረበበትን ይዞታ አስምልክቶ በወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት አዝዟል፡፡ በዚሁ አግባብ የወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ግራ ቀኙ ክስ የቀረበባቸውን ይዞታዎች አስምልክቶ ያውቁልናል የሚሏቸውን ሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ በሽማግሌዎቹ የተነገረውን ቃል በቃለጉባኤ መልክ በማስፈር ውጤቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል እና የቀረበውን ቃለጉባኤ ከመረመረ በኋላ ክስ የቀረበባቸው ይዞታዎች ነባር ይዞታነቱ የአመልካች ወላጅ አባት ሆኖ የአሁን ተጠሪዎች ለአመልካች ወላጅ አባት የእኩሌታ ሲያርሱ የነበረ መሆኑን፤ እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ደግሞ ለአሁን አመልካች ሲያካፍሉ ቆይተው ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ማካፈሉን ትተው ይዞታውን ይዘው እየተጠቀሙበት ያሉ ለመሆኑ አረጋግጫለሁ በሚል ተጠሪዎች ይዞታውን ለቀው ለአመልካች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ ይዞታነቱ የአመልካች አባት ቢሆንም ተከሳሾቹ መብት ካልነበረው ሰው ላይ ገዝተው የያዙ የቅን ልቦና ገገርዎች ስለመሆናቸው ጠቅሶ አመልካች ከፈለገ መብት ሳይኖረው ቤቱን ለተከሳሾቹ የሸጠውን ሰው መክሰስ ይችላል በሚል በሁለቱ ተከሳሾች ላይ የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የአሁን ተጠሪዎች በአንድ በኩል፤ የስር ፍርድ ቤት 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በሌላ በኩል ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያየ መዝገብ ላይ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ሁለቱን የይግባኝ መዝገቦች አጣምሮ ከመረመረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ገድለት አልተገኘም በማለት አፅንቷል፡፡

ተጠሪዎች በድጋሚ ይህንኑ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸው ይዞታዎች በ1982/1983 ተሰጥቷቸው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲጠቀሙበት የነበረ እና በስማቸውም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪዎች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፤ ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን ይዞታዎች በፊት ለአመልካች አውራሽ እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ደግሞ ለአመልካች የእኩሌታ እያረሱ ሲያካፍሏቸው የነበረ ለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር እንደሌለ፤ የአመልካች አውራሽ በሞቱበት 1996 ዓ.ም ጭምር ክስ የቀረበባቸው ይዞታዎች በተጠሪዎች እጅ የነበረ በመሆኑ አውራሻቸው ያልነበራቸውን መብት አመልካች ሊወርሱ አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር አመልካች ከ29 ዓመት በኋላ ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ይህንን በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 04/2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት የአመልካች አባት ከመንግስት የተሰጣቸው ስለመሆኑ መሬት አስተዳደር ገልፆ እያለ እንዲሁም ተጠሪዎች ይዞታውን በህጋዊ መንገድ ስለመያዛቸው ባለረጋገጡበት የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገበት አግባብ በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ መሰረታዊ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ ከመመርመሩ በፊት ጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተጣርቶ የተወሰነ ስለመሆኑ በቅድሚያ መፈተሽ ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንግዲህ ግራ ቀኙ የሚከረከሩት በይዞታ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ የከተማም ሆነ የገጠር ይዞታን አስመልክቶ መረጃዎችን አሰባስቦ የመያዝ፣ ይዞታውን የመለካት፣ የመመዝገብ፣ ባለመብት ለሆኑት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን የመስጠት እና መሰል ሥልጣን እና ተግባር በተዋረድ የሚገኙት የመሬት አስተዳደር አካላት በመሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር ይዞታን አስመልክቶ ለሚነሳ ክርክር ከእነዚህ አስተዳደር አካለት የሚሰጥ ማስረጃ አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የይዞታ ክርክር አስመልክቶ ከአስተዳደር አካል የሚሰጥ ማስረጃ በራሱ ፍፁም እና የመጨረሻ ማስረጃ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ክርክር ከቀረበበት ይዞታ ጋር በተያያዘ የቀረበው መግለጫ እንደየአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል በፍርድ ቤት ክርክር በቀረበበት ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ክፍል እገዛ ካስፈለገ በአስተዳደሩ ተጣርቶ እንዲቀርብ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሞላ ጎደል አስተዳዳር ክፍሉ ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእጁ የሚገኙ ሰነዶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሊሆን እንደሚገባ፣ ከዚህ ባለፈ አስተዳደር ክፍል በፍርድ ቤት በቀረበ ጉዳይ ላይ ምስክር ሰምቶ አልያም በቃለጉባኤ እያጣራ እንዲያቀርብ የሚሰጥ የውክልና ትዕዛዝ አግባብነት እንደሌለው እና አከራካሪው ነጥብ በምስክር የሚጣራ ከሆነ ምስክሮችን አስቀርቦ በሥነ-ሥርዓት ህጉ መሰረት ምስክሮቹን ጠይቆና መርምሮ ማጥራት ያለበት ፍርድ ቤት እራሱ እንጂ ሌላ አካል ስላለመሆኑ ይኸው ችሎት በመ/ቁ/169522 ላይ አስገዳኝ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበት ይዞታን አስመልክቶ በክፍሉ መሬት አስተዳደር በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ከወረዳው መሬት አስተዳደር የተሰጠው ምላሽ ይዞታውን አስመልክቶ በእጁ ያለውን የሰነድ ማስረጃን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ግራ ቀኙ ክስ ስለቀረበበት ይዞታ ያውቁልናል ያሏቸውን ሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ የሽማግሌዎቹን የምስክርት ቃል መሰረት ተደርጎ የተጣራበትን ቃለጉባኤ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ አስመልክቶ ምን ዓይነት ማስረጃ በእጁ እንዳለ እና ከማስረጃው አንፃር ማን ከመቼ ጀምሮ በይዞታው ላይ መብት እንዳቋቋመ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ ፍርድ ቤቱም ከወረዳው መሬት አስተዳደር የቀረበለትም ማስረጃ እና የግራ ቀኙን ማስረጃ መሰረት አድርጎ ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ በፍርድ ሀተታው ላይ የጠቀሰ ቢሆንም ከአስተዳደር አካል ቀርቧል የተባለው የሰነድ ማስረጃ ከላይ የተመለከተው ቃለ ጉባኤ እንደሆነ ከቀረበው የስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ቅጂ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ በዚህ ችሎት ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተጣርቶ ተወስኗል የሚያስብል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ከዚሁ አንፃር ጉዳዩ በድጋሚ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተጣርቶ መወሰን የሚገባው በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/391105 ላይ ህዳር 28/2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/344291 ላይ ጥቅምት 02/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/41151 ላይ ሚያዝያ 21/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የቡራዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/73118 ላይ የካቲት 25/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከአሁን ተጠሪዎች አንፃር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የቡራዩ ወረዳ ፍ/ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የወረዳው መሬት አስተዳደር ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በተመለከተ የተደራጀ ማህደር በእጁ ካለ ከማህደሩ በመመርመር ነባር ይዞታነቱ የማን እንደሆነ፣ በይዞታው ላይ አግባብነት ያለው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማን ከመቼ ጀምሮ እንዳለው፣ ይህ ከሌለ በይዞታው ላይ ግብር በማን ስምና ከመቼ ጀምሮ እየተከፈለ እንዳለ በአግባቡ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝ፣ እና

3. ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተጣርቶ የሚቀርብለትን ሪፖርት ከግራ ቀኙ ክርክር እና ቀድሞ በግራ ቀኙ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ ምስክር በመስማት ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ማስረጃዎቹን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መርምሮ እና መዝኖ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት መዝገቡ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም